

ስህተቱን አሳምነው ምክር ይቀበል ዘንድ

አንዳንድ ሰዎች በግል ፍላጎታቸው በመመራት ብቻ ርባና ቢስ፣ ብዙና ተራ የሆኑ ምክርና ማሳሰቢያዎችን በመስጠት ሰዎችን ያስቸግራሉ። ለምሳሌ፡- ሠርግ ደግሰህ የጠራኸው አንድ ሰው "ውድ ወንድሜ ሠርጉ ጥሩ ሠርግ አልሆነልህም። በከንቱ ነው የደከምከው። በጣም የተዋጣለት ሠርግ ይሆናል ብዬ ነበር የጠበቅኩት" ይልሃል።

"እንዴት?" ብለህ ስትጠይቀው።

"ውድ ወንድሜ አብዛኛው ምግብ ጥብሳ ጥበስ ነው። እኔ በግሌ ጥብሳ ጥበስ አልወድም። የሰላጣ ዘሮችም ሎሚ በጣም ስለበዛባቸው ይመራሉ። ኬኮቹም ክሬም አለባቸው። በአጠቃላይ ብዙ ሰዎች ምግቡን አልወደዱትም። የተመገቡት ይሉኝታ ስለያዛቸውና አማራጭ ስላጡ ነው" ይልሃል። በዚህ አይነቱ አስተያየት ሰጪ እንደምትናደድ ምንም ጥርጥር የለውም። አስተያየቱንም አትቀበለውም። ምክንያቱም የተመሰረተው በግላዊ ጣዕም ላይ ነው። የግሉን ምርጫና አስተያየት ብቻ ተመርኩዞ አንድን ሰው ከልጆቹና ከሚስቱ ጋር ያለው ግንኙነት ምን መሆን እንዳለበት፣ ቤቱን እንዴት መገንባት እንዳለበት፣ ምን ዓይነት መኪና መግዛት እንዳለበት ይመክረዋል።

በግል ምርጫህ ላይ ተመስርተህ ለሰዎች ምክር ከመስጠት ተቆጠብ። አዎ! አንድ ሰው አስተያየት ከጠየቀህ አካፍለው። ነገር ግን የተሳሳተን ሰው ስትመክር ያንን መጠቀም የለብህም። ምናልባትም ምክር የሚሰጠው ሰው መሳሳቱን ላያውቅ ይችላል። ስለዚህ ምክር የምትሰጥ ከሆነ የምታቀርበው ሀሳብ ጠንካራ መሆኑን ማረጋገጥ አለብህ። በአንድ ወቅት አንድ የገጠር ሰው ከደጋግ ሰዎች ጋር ቁጭ ብሎ ነበር። ሰዎቹ ለወላጆች ስለሚደረገው እንክብካቤ ያወራሉ።

ሰውዬው ንግግራቸውን ያዳምጣል። አንደኛው ወደሱ ዞር አለና እከሌ ሆይ! ከእናትህ ጋር ያለህ ግንኙነት ምን ዓይነት ነው? ሲል ጠየቀው።

"በጣም አዝንላታለሁ" ሲል መለሰ።

"እዝነትህን ለማሳየት ምን ታደርግላታለህ?" አለው።

"ወላሂ አንድም ቀን በዱላ መትቻት አላውቅም!" አለ።

ሊመታት ሲፈልግ በእጁ ወይም በጥምጣሙ ነው ማለት ነው የሚመታት። ለሷ ካለው ከፍተኛ እዝነት የተነሳ በዱላ መትቷት አያውቅም። ይህ ምስኪን ሰው ስለ ከፉና በጎ የሚያውቀው ነገር የለም። ስለዚህ የምትመክረው ሰው ስህተቱን ያምን ዘንድ ለስላሳና ትህትት ሁን።

በነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ዘመን አንዲት ሴት ነበረች። ከጎረቤት አንዳንድ ነገሮችን የምትበደርና መመለስን የምትረሳ። ሰዎች ሲያስታውሷት ምንም ነገር አልተበደርኩም በማለት ትከዳለች። ይህ እየባሰባት በመሄዱ ሰዎች ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ዘንድ በመሄድ ምሬታቸውን ገለጹ። ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) እጇ እንዲቆረጥ አዘዙ። ሆኖም ከታላላቅ ጎሳዎች ከአንዱ የተገኘችው ይህቺ ሴት እጇ ሊቆረጥ መሆኑ ቁረይሾችን አስቆጣ። ቅጣቱን እንዲያቀሉላትና ከዚያ ያነሰ ቅጣት ለምሳሌ ግርፋት ወይም የገንዘብ ቅጣት እንዲጣልባት ነብዩን (ሲ.ዐ.ወ) ለማግባባት ወሰኑ። ይህን ሀሳብ ይዞ ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ዘንድ የመጣ ሰው ሁሉ ሳይሳካለት ይመለሳል። ቁረይሾች ነብዩን ለማናገር ከኡሳማ ኢብኑ ዘይድ የበለጠ ሰው እንደሌለ አሰቡ።

ኡሳማ ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) በጣም የሚወዱትና በጣም የሚወዱት ሰው ልጅ ነው። እሱም ሆነ አባቱ ቤታቸው ውስጥ ነው ያደጉት። በመሆኑም እንደ ልጆቻቸው ነው የሚያዩዋቸው። ኡሳማ ወደ አላህ መልዕክተኛ መጣ። እንኳን ደህና መጣህ ብለው ተቀበሉት። ስለ ቅጣቱ ማቅለል ሲያወራ ሴትዮዋ ከተከበረ ጎሳ ውስጥ መሆኗን ጠቀሰ። ኡሳማ ሃሳባቸውን ለማስቀየር ንግግሩን ቀጠለ። ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ያዳምጡታል። ኡሳማ እየጠየቀ ያለው በጭራሽ የማይሆን ነገር መሆኑን ባለማወቅ በሙሉ ልቡ የሚሰጠው ማብራሪያና ክርክር ገርሟቸው ይመለከቱታል። ነብዩ ተቆጡና ፊታቸው ተቀያየረ። በመጀመሪያ እንዲህ በማለት ስህተቱን ጠቆሙት።

"አንዱን የአላህ ህግ እንድጥስ ነው የምትጠይቀኝ?" በኡሳማ ለምን እንደተቆጡ እያብራሩለት ነው። አላህ በባሪያዎቹ ላይ ተግባራዊ እንዲሆን የደነገገው ህጋዊ ቅጣት ላይ ማንም ሰው ጣልቃ መግባት አይችልም። ኡሳማ ስህተቱን በመረዳት ወዲያውኑ "የአላህ መልክዕተኛ! ሆይ ይቅርታን ለምኑልኝ" አላቸው።

ዙሁር ሶላት ላይ ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ከህዝቦቻቸው መሃል በመቆም መመሰገን ያለበትን ካመሰገኑ በኋላ እንዲህ አሉ:- "ከናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦች የጠፉት የተከበረ የሚሉት ሰው ሲሰርቅ በመተዋቸውና ደካማ ሰው ሲሰርቅ ቅጣቱን ተግባራዊ በማድረጋቸው ነው። ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ። የሙሐመድ ልጅ ፋጡማ ብትሰርቅ እጇን እቆርጣታለሁ" በማለት የሴትዮዋ እጅ እንዲቆረጥ

አዘዙ። አኢሻ (ረ.ዐ) ስለዚች ሴት ስትናገር "ከልቧ ተውበት አድርጋ ነበር። ባልም አግብታለች። እኔ ዘንድ ትመጣ ነበር። እኔም የምትፈልገውን ነገር ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እነግርላት ነበር" ብላለች። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ኡሳማ ኢብኑ ዘይድ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር በርካታ ነገሮችን አሳልፏል። ሁሉም የእዝነትና የጥበብ ምሳሌዎች ናቸው። ኡሳማ እንዲህ ይላል፡- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የጁህይናህ ንዑስ ጎሳ ወደሆኑት ወደ አልሁራቃት ላኩን። አሸነፍናቸው እኔና አንድ አንሷር ከነሱ መካከል የሆነ አንድ ሰው አገኘን። ሮጠና በአንድ ዛፍ ተደበቀ። ደረስንበትና ልንመታው ስንል "ከአላህ በስተቀር የሚመለክ ጌታ የለም" አለ። ጓደኛዬ ሰይፉን መለሰ። እኔ ግን ይህን ንግግር የተናገረው እንዳንገድለው ስለፈራ ነው አልኩና ገደልኩት። ሆኖም ይህ ነገር ውስጤን ረበሸኝ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ሄድኩና የተፈጠረውን ነገር ነገርኳቸው።

"ከአላህ በስተቀር የሚገዙት ጌታ የለም እያለ አንተ ገደልከው?" አሉኝ። እኔም "ከልቡ አይደለም ይህን የተናገረው። የያዝነውን መሳሪያ ስለፈራ ነው" አልኳቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጥያቄውን ደገሙት። "ከአላህ በስተቀር የሚገዙት ጌታ የለም እያለ አንተ ገደልከው?" የናንተን መሳሪያ ፈርቶ የተናገረው መሆኑን በርግጠኝነት ለማወቅ ልቡን ከፍተህ አየህ?" አሉኝ። ኡሳማ ዝም አለ። ምክንያቱም ልቡን ከፍቶ አላየም። ሆኖም በጦርነት ላይ ነው የገደለው። ሰውዬውም ታጣቂ ነው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አሁንም ትችቱን ደገሙት። "ከአላህ በስተቀር የሚገዙት ጌታ የለም እያለ አንተ ገደልከው?"

"ኡሳማ ሆይ ሰውዬውን የገደልከው ላኢላሃ አለላህ ሙሐመድ ረሱሉላህ ካለ በኋላ ነው። በፍርዱ ቀን ከአላህ በስተቀር የሚመለክ ጌታ የለም ለሚለው ምስክርነት ምን ምላሽ ልትሰጥ ነው?"

"የዚያን ቀን በሰለምኩ ብዬ እስክመኝ ድረስ ጥያቄውን ደጋገሙት" ይላል ኡሳማ። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ተመልከት። ቀስ በቀስ እንዴት ስህተቱን እንዳብራሩለት፣ እንዳሳመኑት፣ እንደገሰጹትና እንደመከሩት። የምትመክረውን ሰው ማሳመን ትችል ዘንድ አስተሳሰቦቹንና መርሆቹን በተቻለ መጠን ለመሞገት ሞክር። ከሱ አመለካከት በኩል ሆነህ አስብ።

አንዴ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስጊድ ውስጥ በእንከን የለሽ ባልደረቦቻቸው ተከበው ቁጭ ብለው ነበር። አንድ ወጣት ወደ መስጊዱ ገባና የሆነ ሰው እንደሚፈልግ ግራና ቀኝ አማተረ። ከዚያም ዓይኑ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ አረፈና ወደሳቸው መጣ። ወጣቱ ስብስቡን ተቀላቅሎ በመቀመጥ የአላህ ቃል ያዳምጣል ተብሎ ነው የታሰበው።

ሆኖም አይደለም። ወጣቱ ነብዩንና በዙሪያቸው ያሉ ባልደረቦቻቸውን ከተመለከተ በኋላ በድፍረት እንዲህ አለ፡-

"የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ... እንዳደርግ ፍቀዱልኝ።" እውቀት እንዳገኝ? አላለም። ጅሃድ እንድወጣ? አላለም። ምን እንዳለ ታውቃላችሁ? "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ዝሙት እንድሰራ ፍቀዱልኝ" አላቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የቁርዓን አንቀጾችን በመጥቀስና ልቡን ሊነኩ በሚችሉ ቃላት ምክር በመስጠት ሃሳቡን ማጣጣል ይችላሉ። ሆኖም አላደረጉም። የተለዬ መንገድን መረጡ።

"ይህ ነገር በእናትህ ላይ እንዲደርስ ትፈልጋለህ?" ወጣቱ አንድ ሰው መጥቶ እናቱ ላይ ዝሙት ሲፈጽም ታሰበውና እየቀፈፈው "አልፈልግም። ይህ ነገር እናቴ ላይ እንዲደርስ አልፈልግም" አለ።

"ልክ እንዳንተ ሌላውም ሰው በእናቱ ላይ ይህ ነገር እንዲደርስ አይፈልግም አሉት። ከዚያም "በእህትህ ላይ እንዲደርስ ትፈልጋለህ?" በማለት ጠየቁት። ወጣቱ በሚወዳት እህቱ ላይ ዝሙት ሲፈፀምባት አሰበና በድጋሚ እየቀፈፈው "አልፈልግም። ይህ ነገር በእህቴ ላይ እንዲደርስ አልፈልግም" ሲል መለሰ። ነብዩም "በተመሳሳይ ሌሎች ሰዎችም ይህ ነገር በእህቶቻቸው ላይ እንዲፈፀም አይፈልጉም" አሉት። በአክስትህ ላይስ እንዲፈፀም ትፈልጋለህ? ሲሉ ጠየቁት "አልፈልግም... አልፈልግም..." ሲል መለሰ ወጣቱ። ከዚያም "ለራስህ የምትወደውን ነገር ለሰዎችም ውደድ። በራስህ ላይ የምትጠላውን ነገር በሌሎች ላይም ጥላ" አሉት። ወጣቱ እንደተሳሳተ ተገነዘበና "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አላህ ልቤን እንዲያፀዳው ለምኑልኝ" አላቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደሳቸው አስጠጉትና እጃቸውን ደረቱ ላይ አድርገው "አላህ ሆይ ልቡን ምራው። ኃጢያቶቹን ይቅር በለው። መታቀብን ስጠው" በማለት ዱዓ አደረጉለት። ወጣቱም "ወደ አላህ መልዕክተኛ ስሄድ ዝሙት ለኔ በጣም ተወዳጅ ድርጊት ነበር። ከሳቸው ተለይቼ ስወጣ ግን ዝሙት በኔ ዘንድ የሚጠላ ተግባር ሆነ" እያለ ወጣ። ተመልከት ምን እንዳደረጉለት። ወደኔ ና አሉት። እጃቸውን ደረቱ ላይ በማስቀመጥ ዱዓ አደረጉለት። ነብዩ የሰዎችን ስህተት ለማረም ያሉ እድሎችን በሙሉ ይጠቀማሉ። ይህን ያደረጉት የድርጊቱን መጥፎነት ካሳመኑት በኋላ ነው። በራሱ ፍላጎት ነው ለመተው የወሰነው። ስለሆነም ያንን መጥፎ ድርጊት ድጋሚ አይተገብረውም።

ህግ...

መጥፎ ድርጊትን የሚፈጽመው ሰው የድርጊቱን መጥፎነት የሚረዳ ከሆነ ምክር እንደሚያስፈልገው ያምናል። ስለዚህ ምክር ተቀባይ ይሆናል።



አትተችኝ! የታሪኩ መጨረሻ?

አንዳንዶች በጥቃቅን ስህተቶች ሰዎችን በመተቸት ከነሱ የቀረቡና የራሳቸውን ስብዕና ያጠነከሩ ይመስላቸዋል። እውነታው ይህ ነው። በሰዎች ላይ የማያቋርጥ ውርጅብኝና ትችት ማቅረብ ብልህነትን አያረጋግጥም። በተቃራኒው ይህን በተቻለ መጠን መተውና ሰዎችን በማይጎዳና በማያሳፍር መልኩ ማረም የብልህነት ማሳያ ነው። በተለይ በዓለማዊ ጉዳዮችና ግላዊ ሙበቶች ላይ ቸልተኛ መሆን ተመራጭ የሚሆንባቸው ሁኔታዎች ብዙ ናቸው።

አይችልም ሞኝ ሰው አገርን ሊመራ
ሞኝ የሚመስለው ነው ይህን የሚሰራ።

ትችት የሚደርስበት ሰው ትችትን ወደሱ እንዳነጣጠረ ሹል ቀስት ነው የሚመለከተው። ምክንያቱም ራሱን ጎደሎ አድርጎ ያስባል። ይህ ነው የመጀመሪያው ነጥብ። ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ ሰዎች ባሉበት ምክር ላለመስጠት መሞከር ነው።

ብቻዬን አድርገህ ለግሰኝ ምክርህን
ከሰዎች ጋር ስሆን ተወኝ እባክህን
ምክር ከሰው መሃል ነውና ዘለፋ
አንዱንም አልይዘው ይልቁን አትልፋ::

ስህተት በጣም ሲሰፋፋ ካዩህና በሰዎች መካከል ምክር መስጠት ግድ ከሆነብህ ከዚህ በፊት ለመግለፅ እንደሞከርነው ቀጣዩን መርህ ተጠቀም። "ይህን ይህን የሚያደርግ ሰው ምን ነካው?" በል። ትችት ተቺው የተሳቺውን ጀርባ እንደሚገርፍበት ጅራፍ ነው። አንዳንድ ሰዎችን ትችትን በማብዛት ወይም ያለፉ ነገሮችን አንስተው በመተቸት ሰዎችን ያርቃሉ። ትችታቸው ምንም ዓይነት ስህተትን ሳያርም ወይም ምንም ዓይነት ዓላማን ሳያሳካ።

አንድ ሌላ አገር ሄዶ የጭነት መኪና ሹፌር በመሆን የሚሰራ ምስኪን ሰው ነበር። መኪናው ውስጥ ገባና ረጅም ጉዞ ጀመረ። በጣም ከመድከሙ የተነሳ በመንገድ ላይ እያለ እንቅልፉ መጣ። ከእንቅልፉ ጋር እየታገለ ቶሎ ለመድረስ ፍጥነቱን በመጠኑ ጨመረ። ሙሉ ትኩረት መስጠት ባይችልም መኪናውን እየነዳ ነው። ከፊት ለፊቱ ሶስት ሰዎችን የጫነች ትንሽ መኪና መጣች። ከፉኛ ገጫት። አካባቢው በአቧራና ጭስ ተሞላ። በዚያ የሚያልፉ ባለ መኪኖች መኪኖቻቸውን

እያቆሙ አደጋውን ይመለከቱ ጀመር። የጭነት መኪናው ሹፌር ከመኪናው ወርዶ የገጨውን መኪና ሲመለከት ሶስቱም ሰዎች ሞተዋል። ሰዎቹ የሚኾቹን ሬሳ ከመኪናው ውስጥ ካወጡ በኋላ አምቡላንስ ጠሩ። እሱም ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹ ይዞ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብሎ የአምቡላንሱን መምጣት በጭንቅት ይጠባበቅ ጀመር። ስለ እስር ቤት ህይወቱ፣ ስለ ደም ካሳ፣ ስለ ህፃናት ልጆቹና ስለሚስቱ እጣ ፈንታ ያስባል። የመከራ ተራራ ላዩ ላይ ተጫነበት። በዚያ መንገድ የሚያልፉ ሰዎች ሁሉ የስድብና የእርግማን መዓት ያወርዱበታል። ይገርማል! አሁን በዚህ ሰዓት በዚህ ምስኪን ሰው ላይ ትችት ማቅረብ ምን ጥቅም አለው?

◊ እስቲ ምን አንቀዠቀዠህ? ባትፈጥን ኖሮ እንዲህ አይነት ከባድ አደጋ ባላደረስክ ነበር።

◊ እርግጠኛ ነኝ ተኝተህ ነበር የምትነዳው። ምናለ መኪናውን አቁመህ ብትተኛ ኖሮ?

◊ እንደ አንተ ዓይነት ሰው በጭራሽ የመንጃ ፈቃድ ሊሰጠው አይገባም ነበር! ...

ሁሉም የሚያናግሩት በጩኸትና በቁጣ ነው። ይህን ሁሉ ነገር የመቋቋም አቅም አጣ። ከተቀመጠበት ድንጋይ ላይ ተንሸራቶ መሬት ላይ ወደቀ። እስከወዲያኛው አሸለበ። ጭካኔ በተሞላበት የበዛ ትችታቸው አሰቃይተው ገደሉት። ዝም ቢሉት ኖሮ ለሱም ሆነ ለነሱ የተሻለ ይሆን ነበር።

ራስህን ትችት ከሚደርስበት ሰው ጫማ ውስጥ አስቀምጥ። ነገሮችን ልክ እንደሱ ሆነህ ተመልከታቸው። ምናልባትም አንተ በሱ ቦታ ብትሆን ከሱ የበለጠ ስህተት ልትሰራ ትችል ይሆናል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህን ነገር ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። ከባልደረቦቻቸው ጋር ከኸይበር ሲመለሱ ረጂም መንገድ ተጉዘው ደክሟቸው ነበር። ሲመሽ አንድ ቦታ ላይ ለሙተኛት አረፉ። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) "ተረጋግተን እንተኛ ዘንድ ለሱብሂ ሶላት እንደሚነቃ እርግጠኛ የሆነ ማነው?" በማለት ጠየቁ። ቢላል (ረ.ዐ) በጉጉት "እኔ እቀሰቅሳችኋለሁ የአላህ መልዕክተኛ!" አለ። ሁላቸውም ተኙ። ቢላል ተነስቶ እስኪደክመው ድረስ ዱዓ አደረገ። በረጂም ጉዞ የተነሳ እሱም ደክሞት ነበር። ትንሽ አረፍ ለማለት ግመሉን ተደግፎ ቁጭ አለ። የሱብሂ ሶላት ወቅት ሲገባ ሊቃተውና ተኛ። ሁላቸውም በጣም ስለደከማቸው ጥልቅ እንቅልፍ ተኝተዋል። ምሽቱ ሄዶ ንጋት መጣ። ሁሉም እንደተኙ ናቸው። የፀሐይ መውጫት ሲነካቸው ከእንቅልፋቸው ነቁ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ነቁ። ባልደረቦቻቸውም እንዲሁ። ፀሐይዋን ሲመለከቱ ግራ ተጋቡ። ሁሉም ሰው ቢላልን ይመለከት ጀመር።

ነብዩም "ምን ዓይነት ስራ ነው የሰራኸው ቢላል?" በማለት ጠየቁት። ቢላልም በተፈጠረው ነገር እንዲህ ሲል መልስ ሰጠ። "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ነፍሳችሁን

በወሲደው የኔም ነፍስ ተወሰዳ ነበር" አላቸው። ማለትም እኔ ሰው ነኝ። እንቅልፌን ለማሸነፍ ጥረት አድርጌ ነበር። ነገር ግን አልቻልኩም። ልክ እንደናንተ ሁሉ እኔም በእንቅልፍ ተሸነፍኩ ማለቱ ነው። ኑብዩም (ሰ.ዐ.ወ) "እውነቱን ተናገርክ" አሉና ገዘም አሉ። በዚያ ሁኔታ ላይ ይህን ሰው መወቀሱ ምን ጥቅም አለው?

ኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "እንንቀሳቀስ!" አሉ። ተንቀሳቀሱ። ትንሽ ከተጓዙ በኋላ አንድ ቦታ ላይ አረፉ። ውዱዕ አደረጉ። በነብዩ አሰጋጅነት ሰገዱ። ሶላቱ ሲጠናቀቅ ለባልደረቦቻቸው "ረስታችሁ ሶላት ካሳለፋችሁ ትገ ባላችሁ ጊዜ ወዲያውኑ ስገዱ" አሏቸው። ምን ዓይነት ብልህ ሰው ናቸው! ለማንኛውም መሪ የትምህርት ማዕከል ሆነው ያገለግላሉ። የዘመናችን መሪዎች ሰዎችን መወቀስና መገሰጽ ነው ስራቸው። ኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ራሳቸውን በስራቸው ባሉ ሰዎች ጫማ ስር ያስቀምጣሉ። በነሱ ቦታ ሆነው ያስባሉ። ከአካል ጋር ከመገናኘታቸው በፊት ከልቦች ጋር ይገናኛሉ። ደካማ የሆኑ የሰው ልጆች አንጂ ማሽኖች አለመሆናቸውን ይገነዘባሉ።

በሂጅራ በዘጠነኛው ዓመት ሮማኖች ኑብዩን (ሰ.ዐ.ወ) በሶሪያ አቅጣጫ ለመውጋት ጦር አሰባስበው ነበር። በወቅቱ ኑብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ከነሱ ጋ ለመዋጋት ጦር አሰባስበው ነበር ይባላል። ሶስት ሺ ተዋጊዎችን ሰበሰቡ። የጦር መሳሪያና ስንቅ ሰጧቸውና "መሪያችሁ ዘይድ ቢን ሀሪዛህ ነው። እሱ ከተሰዋ ጀዕፈር ቢን አቡ ጣሊብ ይመራችኋል። እሱ ከተሰዋ ደግሞ የሚመራችሁ አብዱላህ ቢን ረዋሃ ነው" አሉ። ኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወጡና "አላህ ከናንተ ጋር ይሁን፤ አላህ ይጠብቃችሁ። በሰላም ይመልሳችሁ" በማለት ዱዓ አድርገው ሸኟቸው። አብዱላህ ቢን ረዋሃ መስዋዕት ለመሆን ጓጉቶ ስንኞቹን ይደረድር ነበር። ጦሩ ወደ መአጣህ ወጊያ ገሰገሰ። ሶሪያ ውስጥ ማአን የሚባል ቦታ ላይ ሰፈሩ። የሮማውን ንጉስ ሄራክለስ ሶሪያ ውስጥ መቶ ሺ የሮማ ወታደሮችንና መቶ ሺ የነሳ ተዋጊዎችን በአጠቃላይ ሁለት መቶ ሺ ጠንካራ ጦር እንዳዘጋጀ ተሰማ።

መስሊሞች የዜናውን እውነትነት ሲያረጋግጡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በማሰብ ሁለት ቀን ቆዩ። "የጠላቶቻችንን ቁጥር ለኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በደብዳቤ ማሳወቅ አለብን። ተጨማሪ ጦር ይልኩልናል። አለያም የሆነ ነገር እንድናደርግ ያዙናል። እሳቸው የሚሉንን ነገር እንፈጽማለን" ይባባላሉ።

ሁሉም የየራሱን አስተያየት ሲሰጥ አብዱላህ ቢን ረዋሃ ተነሳና "ሰዎች ሆይ የጠላችሁት ነገር ቢኖር መጀመሪያ ፊልጋችሁት የመጣችሁትን በአላህ መንገድ መስዋዕት መሆን ነው። አሁን ከሱ ለመሸሽ እየሞከራችሁ ይመስለኛል። ሰዎችን የምንዋጋቸው በኃይልና በቁጥር አይደለም። አላህ በሰጠን ኃይማኖት እገዛ ነው። እንሂድ። ሁለት ጥሩ ኢጋጣሚዎችን እናገኛለን። ድል ወይም ሸሂድነት!" አለ። የሮማ ወታደሮች ወደ ሰፈሩበት ወደ መአጣህ ሄዱ። በበርካታ ቁጥርና በጠንካራ ኃይል ተደራጅተው አገኟቸው።

አቡ ሁረይራ ሲናገሩ መአጣ ላይ ተገኝቼ ነበር። ሮማዎች በቁጥርም፣

በጌጣጌጥ፣ በሀርና በወርቅ አሸብርቀዋል። ኢይኔን አንጸባረቀኝ። ሳቢት ቢን አርቀም "በድር ጦርነት ላይ ከኛ ጋር አልተገኘህም። በቁጥር አላሸነፍናቸውም" አለኝ። ጦሮቹ ተገናኙና ውጊያው ተጀመረ። ዘይድ ቢን ሀሪሳህ የአላህ መልዕክተኛን ባንዲራ ይዞ ተዋጋ። አካሉ በበርካታ ጦሮች እስኪቆራረጥ ድረስ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተሰዋ። ጀዕፈር በሚያምር ፈረሱ በሙሉ ወኔ ባንዲራውን በግራ እጁ ይዞ ተዋጋ። ግራ እጁ ተቆረጠ። በቀኝ እጁ ያዘው። እሱም ተቆረጠ። ከዚያም ባንዲራውን በክንዱ ያዘው። በመጨረሻ ተገደለ። እድሜው ሰላሳ ሶስት ነበር። ኢብን ኡመር ሲናገሩ "የጀዕፈርን ሬሳ አይቼዋለሁ። አምሳ ቦታ ላይ ተወግቶ ነበር። ሁሉም ከፊት ለፊቱ የተመታቸው ናቸው ብለዋል። አላህ በጀነት ሁለት ክንፎችን ይተካለታል። ወደ ፈለገው ቦታ ይበርበት ዘንድ። አንድ የሮማ ወታደርም አካሉን በሰይፍ ለሁለት ከፍሎታል።" ጀዕፈር ሲገደል አብዱላህ ቢን ረዋሃ ባንዲራውን አነሳና ወደፊት ሄደ። ሆኖም ወደ ጠላቶቹ ለመሄድ አምታታና እንዲህ አለ:-

"ነፍሴ ሆይ! ትዋጊያለሽ ብዬ ምያለሁ። ትዋጊያለሽ። ለመዋጋት ትገደጃለሽ። ሰዎች ተሰባስበው የጦርነት ለቅሶ ሲያለቅሱ። ለምን ጀነት መግባትን ስትጠይ አይሻለሁ?" ከዚያም ከፈረሱ ላይ ሲወርድ የአጎቱ ልጅ የስጋ አጥንት ይዞ መጣና "ይሄን ብላ ሰሞኑን በጣም ብዙ ስቃይ ደርሶብሃል" አለው። ተቀበለና ትንሽ እንደበላ ከአንድ አቅጣጫ ድምፅ ሰማ። የሚበላውን አጥንት እየተመለከተ "አንተም የዚህ ዓለም ነህ።" በማለት ወረወረውና ሰይፉን ይዞ እስኪገደል ድረስ ተዋጋ። አሁንም ባንዲራው ወደቀ። ሙስሊሞች ግራ ገባቸው። ካፊሮቹ ተደሰቱ። ባንዲራው በአቧራ ተሸፈነ። ድንገት ጀግናው ሶሃባ ሳቢት ቢን አርቀም መጣ:: ባንዲራውን አነሳና "ሙስሊሞች ሆይ! ባንዲራውን ይዣለሁ። መሪያችሁን ምረጡ" አላቸው።

"አንተ መሪ ሁን" አሉት። "አልሆንም" አለ ሳቢት።

ኻሊድ ኢብኑ ወሊድን መረጡ። ባንዲራውን ይዞ በጽናት ተዋጋ። "በሙአጣህ ጦርነት ዘጠኝ ሰይፎች እጄ ላይ ተሰብረዋል። አንድ የየመን ሰይፍ እስኪቀረኝ ድረስ" በማለት ይናገራል። ኻሊድ ጦሩን ወደ ካምፕ ወሰደ። ሮማኖችም እንዲሁ።

ኻሊድ ዛሬውኑ ወደ መዲና ከተመለሰን ሮማኖች ሊከተሉን ይችላሉ ሲል ፈራ። ከእንቅልፋቸው ሲነቁ ኻሊድ የጦሩን አሰላለፍ በመቀየር ፊት ለፊት የነበሩትን ወደ ኋላ ወደ ቀኝ የነበሩትን ወደ ግራ በማቀያየር አሰለፈ። ጦርነቱ ሲጀመርና ሮማኖች ሲመጡ ከሙስሊሞች መካከል አዳዲስ ፊቶችንና አዳዲስ ባንዲራዎችን ተመለከቱ። ግራ ተጋቡና "ትናንት ማታ ተጨማሪ ጦር ሳይመጣላቸው አይቀርም" በማለት በፍርሃት ራዱ። ሙስሊሞች በርካታ ሰዎችን ገደሉ። ከሙስሊሞቹ ወገን አስራ ሁለት ሰው ሞተ።

ኻሊድ ጦሩን ይዞ ወደ ኋላ በማፈግፈግ ወደ መዲና ተመለሰ። መዲና ሲደርሱ ሴቶችና ህፃናት "እናንተ ቦቅቧቆች በአላህ መንገድ ልትዋጉ ሄዳችሁ ሽሽታችሁ ትመጣላችሁ?" በማለት ከመሬት ላይ አቧራ እያነሱ ፊታቸው ላይ ይበትኑባቸው